ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# ፀረ-ሙስና

ፀረ-ሙስና ቅጽ 2 ቁጥር 33 ጥር 15/2018 ዓ.ም

## በውስጥ ገፆች

ዘላቂ የትውልድ ሥነምግባር ግንባታ ላይ በትኩረት እየተሠራ ነው

ገጽ 2

በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ከ47 ሚሊየን ብር በላይ ከምዝበራ ማዳን ተቻለ

ገጽ3

ተማሪዎች ባለመኮረጅ ሙስናን ሊታገሉ ይገባል!

ገጽ 5

የታማኝነት ተምሳሌት፡ ሳጅን ዋሲይሁን በፈቃዱ

ገጽ 6

## በሙስና ሕዝቡን ማማረር ሳይሆን የተሰጠውን ዕድል ተጠቅሞ መስራት ይገባል - ጠ/ሚ አብይ አህመድ(ዶ/ር)









የመንግሥት ሥልጣን የያዘ እና ከሕዝብ ኃላፊነት የተቀበለ አካል መሬት በመሸጥ እና በሙስና ሕዝቡን ማማረር ሳይሆን የተሰጠውን ዕድል ተጠቅሞ ገንዘብ አሰባስቦ አቅም ላነሣቸው የኅብረተሰባችን ክፍሎች ቤት መሥራት መለመድ ያለበት ሥራ መሆኑን ገልጸዋል::

ጠቅላይ ሚኒስትሩ የክረምት በጎ አድራጎት መርሐ-ግብርን ወደ ላቀ ከፍታ ያሸጋገረውን የቱሉ አራራ የተቀናጀ ሞዴል መንደርን መርቀው ሲከፍቱ በሰጡት ገለጻ፣ ይህ ተግባር ሥልጣን ላይ ካለ ሁሉም ሰው በፖለቲካውም፣ በሞራልም፣ በሃይማኖትም የሚጠበቅ ተግባር ነው::

ሥልጣን ለተወሰነ ጊዜ የሚሰጥ እና የሚወሰድ በመሆኑ ሥልጣኑ የተወሰደብን ቀን ከመቆጨት በሥልጣን ዘመናችን እንደየአቅማችን የአምስትም፣ የዐሥርም ሰዎችን ሕይወት በመለወጥ ሕዝባችንን አስደስተን፣ ለራሳችንም ተደስተን፣ ሕዝባችንን ከችግር አውጥተን በምርቃት እንዲሸኙን ማድረግ መቻል ታላቅ ዕድል ነው” ሲሉ ነው የገለጹት::

ከወረዳ አመራር ጀምሮ በየደረጃው ያሉ የመንግሥት ኃላፊዎች ይህንን ሁልጊዜ በልቦናቸው ማሳደር እና በዚሁ አግባብ መሥራት እንዳለባቸውም አሳስበዋል::

እጅ እና ልባችንን ንፁህ አድርገን ስንሠራ እንደዚህ ዓይነት መልካም ነገር ለሕዝባችን እናበረክታለን” ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፣ ከሕዝባችን መስረቅ ስንጀምር ግን እየተጠላላን፣ አንዳችን ሌላችንን እያስለቀስን፣ እርስ በርስ በመጠላለፍ አንድነታችንን እንንዳለን፤ እንደ ሀገርም ልናተርፍ ከምንችለው በተቃራኒው ወደ ኋላ እየቀረን ስለምንሄድ ዕድሉን አግኝታችሁ ሥልጣን ላይ ያላችሁ ሰዎች ሁልጊዜ ማሰብ ያለባችሁ ይህንን ነው” ሲሉ መክረዋል::

## ኮሚሽኑ በ22ኛው ዓለም ዓቀፍ የፀረ-ሙስና ቀን የተከናወኑ የንቅናቄ ሥራዎችን ግምገማ አደረገ

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በ22ኛው ዓለም ዓቀፍ የፀረ-ሙስና ቀን የተከናወኑ የንቅናቄ ሥራዎችን ከተቋማት የሥነምግባር እና ፀረ-ሙስና ሥራ አስፈጻሚዎች ጋር ግምገማ አድርጓል::

በመድረኩ በመንግሥት ተቋማት፣ በልማት ድርጅቶች እና በሕዝባዊ ተቋማት የሥነምግባር እና ፀረ-ሙስና ሥራ አስፈጻሚዎች ጋር በ22ኛው ዓለምአቀፍ የፀረሙስና ቀን በዓል አከባበር ወቅት የተካሄደው የፀረ-ሙስና ትግል የንቅናቄ ሥራ እና የተቋማት መሪዎች ሀብታቸውን ከማሳወቅ አንጻር ያሳዩት ቁርጠኝነት እንዲሁም ዘርፍ-ተኮር የፀረ-ሙስና ትግል አቀጣጥሎ የመቀጠል ሁኔታ ተገምግሟል::

በመሆኑም፣ ዘርፍ-ተኮር የፀረ-ሙስና ንቅናቄ ሰነድ ላይ የተቋማትን የሙስና ተጋላጭነት እና ሥጋት በአግባቡ ያመላከተ እና ንቅናቄው በየዘርፉ በተቋማት ባለቤትነት መቀጠል ያለበት መሆኑን ተመልክቷል::

የፌዴራል መንግስት ከፍተኛ አመራሮች ሀብታቸውን ለማሳወቅ እና ለማስመዝገብ የላቀ ቁርጠኝነት እንዳሳዩ፣ ህዝባዊ ድርጅቶችም ከወትሮው በተለየ ሁኔታ የፀረ-ሙስና ትግል ለማጠናከር የተነቃቁበት መሆኑ መገንዘብ ተችሏል::

መንግስት ሌብነትን መቀነስ ብሎም ማስወገድ ላይ የተጠናከረ ትግል እንዲካሄድ አቅጣጫ አስቀምጦ ርብርብ እየተደረገ ካለው አንጻር፣ የተጀመረው ዘርፍ-ተኮር የፀረ-ሙስና ትግል አጠናክሮ ለመቀጠል የሁሉም ተቋማት የሥነምግባር እና ፀረ-ሙስና ሥራ አስፈጻሚዎች መግባባት ተፈጥሯል::










የሙስና ወንጀል ጥቆማ ካልዎት NCRS ሞባይል መተግበሪያ በመጠቀም ባሉበት ሆነው ይጠቁሙ!

# ዘላቂ የትውልድ ሥነምግባር ግንባታ ላይ በትኩረት እየተሠራ ነው - የተከበሩ አቶ አዝመራ አንደሞ

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሥነምግባር ግንባታ እና ሙስና መከላከል ሥልጠና ጥራትና ተገቢነት አሰራር ስርዓት ላይ የባለድርሻ አካላት የምክክር መድረክ አካሂዷል።









በምክክር መድረኩ የተገኙት በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የዲሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ም/ሰብሳቢ የተከበሩ አቶ አዝመራ አንደሞ እንደ ሀገር በትውልድ ሥነምግባር ግንባታ ላይ በትኩረት እየተሠራ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

የተከበሩ አቶ አዝመራ በንግግራቸው በለውጡ መንግስት ተቋማዊና ስርዓታዊ ሙስና የለም፤ ለዚህም የሚሠሩ ሀገራዊ ፕሮጀክቶች ማሳያ ናቸው ብለዋል።

የብልጽግና ጉዟችንን የሚያደናቅፉ የሞራል ዝቅጠቶችን በስልጠናና ግንዛቤ በመፍጠር እያስተካከልን ግለሰባዊ ሙስናን መቀነስ አለብን፤ ለዚህ ደግሞ የሁላችንም ትብብርና ቁርጠኝነት ያስፈልጋል ሲሉ አጽንኦት ሰጥተዋል።

የኮሚሽኑ ኮሚሽነር ሳሙኤል ኡርቃቶ (ፒኤችዲ) በበኩላቸው በኢትዮጵያ የፀረ-ሙስና ትግል የትውልድ ሥነምግባር ግንባታ፣

ሙስናን አስቀድሞ መከላከልና ህግ ማስከበርን አቀናጅቶ እየተሰራ መሆኑን ጠቅሰው፥ የስልጠና የአሰራር ስርዓት ምን መሆን አለባቸው የሚለው በትኩረት እየተሰራ መሆኑን ተናግረዋል።

የፀረ-ሙስና ትግሉን ለማቀጣጠልና ውጤታማ ለማድረግ የሁሉም ተቋም ትብብርን የሚጠይቅ በመሆኑ ተቋማት ሙስና መከላከልን የእቅዳቸው አካል አድርገው በባለቤትነት መስራት አለባቸው ያሉት ደግሞ በኮሚሽኑ የሥነምግባር ግንባታ ዘርፍ ም/ኮሚሽነር አቶ ፍቃዱ ሰቦቃ ናቸው።

በመድረኩ "ሥነምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥና የጥቅም ግጭትን መከላከል እና የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሙስና መከላከል" በሚል የተዘጋጁ ሁለት የማሰልጠኛ ሞጁሎች ቀርበው ውይይት የተደረገባቸው ሲሆን፥ ለግብዓት የሚሆኑ ሀሳቦችና አስተያየቶች ከተሳታፊዎች ተነስተው ምላሽና ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል።በግምገማ መድረኩ የዲሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ምሁራን፣ የተቋማት የሥነምግባርና ፀረሙስና ሥራ አስፈጻሚዎች፣ የኮሚሽኑ የሥራ ኃላፊዎችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ተሳትፈዋል።


# ኮሚሽኑ ከክልልና ከተማ አስተዳደር ኮሚሽኖች ጋር በቨርቿል ውይይት አካሄደ

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከክልልና ከተማ አስተዳደር የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች ጋር በቨርቿል ኮንፈረንስ አካሄዷል።



ኮንፈረንሱ የሙስና መከላከል ጥናት ዘርፍ በ2018 በጀት ዓመት የመጀመሪያ የ6 ወራት የተከናወኑ አገርዓቀፍ ሥራዎች ላይ ትኩረት ያደረገ ሲሆን፥ በሙስና መከላከል ጥናት፣ በአስቸኳይ ሙስና መከላከል፣ በሀብት ምዝገባና በጥቅም ግጭት መከላከል የተከናወኑ ተግባራት ቀርበው ውይይት ተካሂዶባቸዋል።





በኮንፈረንሱ የተገኙት የሙስና መከላከል ጥናት ዘርፍ ም/ኮሚሽነር አቶ እሸቴ አስፋው እንደ ሀገር በግማሽ በጀት ዓመቱ የተከናወኑ ስራዎች አበረታች መሆናቸውን ጠቅሰው፥ ከዚህ የበለጠ ለመስራትና የፀረ-ሙስና ትግሉን ውጤታማ ለማድረግ በቅንጅት መስራት እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል።

ም/ኮሚሽነሩ አክለውም በስድስት ወሩ የተሰሩ ተግባራት በእቅዱ መሠረት መከናወናቸውን ገልጸው፥ ለዚህም የኮሚሽኑ ድጋፍና ክትትል ውጤት ነው ብለዋል።

በውይይቱ በስድስት ወሩ የነበሩ ጠንካራ ጎኖችና የታዩ መልካም ተሞክሮዎች እንዲሁም የቀጣይ ትኩረት አቅጣጫዎች ተመላክተዋል።

## በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ከ47 ሚሊየን ብር በላይ ከምዝበራ ማዳን ተቻለ

በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል በተጠናቀቀው ግማሽ የበጀት ዓመት ከ47 ነጥብ 5 ሚሊየን ብር በላይ የሕዝብና የመንግሥት ሀብት ከምዝበራ ማዳንና በኦዲት ግኝት ማስመለስ ተችሏል።

የክልሉ የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ሙሉሰው ዘውዴ እንዳሉት፤ በመንግሥትና በሕዝብ ተቋማት ውስጥ የሚፈፀሙ ብልሹ አሠራሮችን ለመከላከል ሕዝብን ያሳተፈ ሥራ እየተሠራ ነው።

ሙስናና ብልሹ አሠራርን በመከላከል ረገድ የሕብረተሰቡ ግንዛቤና ትብብር እያደገ መምጣቱንም ገልጸዋል።

ለአብነትም በተጠናቀቀው ግማሽ የበጀት ዓመት 659 ጥቆማ ከሕብረተሰቡ መቅረቡን ጠቅሰዋል።

በዚህም መሠረት ለ171 ጥቆማዎች አስቸኳይ የመከላከል ሥራ እና ለ138 ጥቆማዎች አሥተዳደራዊ ርምጃ በመውሰድ መፍትሔ መሰጠቱን አረጋግጠዋል።

በአስቸኳይ ሙስና መከላከልና በኦዲት ግኝት ከ47 ሚሊየን 560 ሺህ ብር በላይ የመንግሥትና የሕዝብ ሀብት ከምዝበራ ማዳን መቻሉንና ተመዝብሮ የነበረም በኦዲት ግኝት እንዲመለስ መደረጉን ተናግረዋል።

ከዚህ ውስጥ 25 ሚሊየን 444 ሺህ ብር በቅድመ መከላከል ከምዝበራ መዳኑንና ቀሪው በኦዲት ግኝት መመለሱን ገልጸዋል።

በተጨማሪም 13 ሺህ ካሬ ሜትር የከተማ እና 166 ሔክታር የገጠር መሬት በሙስና ቅድመ መከላከል ሥራ ማዳን ተችሏል ብለዋል።

በሌላ በኩል የ1 ሺህ 281 ሠራተኞችንና 120 ከፍተኛ የመንግሥት አመራሮችን ሀብት በአዲስ የመመዝገብ ሥራ መከናወኑን አመላክተዋል።



## ሃስተኛ ሰነድ ይዞ አገልግሎት የጠየቀ ግለሰብ በህግ ቁጥጥር ስር እንዲውሉ ተደረገ

ሃሰተኛ የጋብቻ ሰነድ በመያዝ በአዲስ መሶብ ዋና መስርያ ቤት የማረጋገጫ አገልግሎት ለማግኘት የጠየቀ ተገልጋይ በፖሊስ ቁጥጥር ስር እንዲውል ተደርጓል።

በዋና መስርያ ቤት ሃሰተኛ የጋብቻ ሰነድ በመያዝ የቀረበው ግለሰብ አገልግሎቱን ከማግኘቱ በፊት በሚደረገው የሰነድ ማጥራት ሃሰተኛ ሰነድ የያዘ ስለመሆኑ በሙያተኞች ተረጋግጧል። ተቋሙ ከከተማው የሲቪል ምዝገባ እና የነዋሪነት አገልግሎት ኤጀንሲ ጋር በጋራ በመሆን ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ክትትል የሚያድረግ መሆኑን አሳውቋል።

አዲስ መሶብ በቅርብ አገልግሎት የጀመረ የአንድ ማዕከል አገልግሎት ሰጪ ተቋም ቢሆንም ብቁ እና የሰለጠኑ ሙያተኞች እንዲሁም ህገ-ወጥነትን በመከላከል ህገ-ወጥ ግለሰቦች በተቋሙ ውስጥ እና በዙርያው ማጭበርበርን እንዳይፈፅሙ ጥብቅ ክትትል የሚያደርግ አደረጃጀት ያለው መሆኑን በመገንዘብ ወደ አዲስ መሶብ የሚመጣ ማንኛውም ተገልጋይ እራሱን ከመሰል ህገ-ወጥነት አፅድቶ እንዲመጣ አሳስቧል።

ህገ-ወጥነትን በመከላከል ዙርያ አዲስ መሶብ የሚወሰደው እርምጃ አስተማሪ ሊሆን በሚችል መልኩ አበክሮ የሚሰራ መሆኑን እናሳውቃለን ብለዋል።




## ኮሚሽኑ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 1 ስር ለሚገኙ ድጋፍ ለሚሹ ዜጎች የአልባሳት ድጋፍ አደረገ

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 1 ስር ለሚገኙ ድጋፍ ለሚሹ ዜጎች የአልባሳት ድጋፍ አድርጓል።



በኮሚሽኑ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ አካትቶ ትግበራ ሥራ ክፍል አስተባባሪነት ለ20 ህፃናት እና ለ50 የአዋቂዎች የተለያዩ አልባሳትን ከኮሚሽኑ አመራሮችና ሠራተኞች በመሰብሰብ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 1 ስር ለሚገኙ ድጋፍ ለሚሹ ዜጎች መስጠት ተችሏል።





## ከግብር ከፋይ ጉቦ ሲቀበል እጅ ከፍንጅ የተያዘ የኦዲት ባለሙያ በቁጥጥር ስር ዋለ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ የገቢዎች ቢሮ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የታክስ ኦዲት ቡድን አስተባባሪ እና የታክስ ኦዲተር ባለሙያ በግብር ከፋይ የቀረበ የወጪ ሰነድ "አንቀበልም" በማለት ጉቦ ሲቀበሉ እጅ ከፍንጅ መያዛቸው ተነግሯል።

ቢሮው ተጠርጣሪ ግለሰቦቹ ግብር ከፋዩ ለኦዲት ምርመራ የሚውል ሰነድ አሟልቶ አቅርቦ እያለ "አላቀረብክም" በሚል የተሰጣቸውን ኃላፊነት ወደ ጎን በመተው ጉቦ መጠየቃቸውን ገልጿል።

ግብር ከፋዩ 3 ሚሊዮን ብር ወጪ የያዙ ሰነዶች ማቅረቡን በመግለፅ "የቀረቡ ሰነዶች እንደ ወጪ አንይዝልህም" በማለት ግብር ከፋዩን ከአንድ ወር በላይ ማመላለሳቸውንም ጨምሮ አሳውቋል።

ሆኖም ግብር ከፋዩ የተጠየቁት ገንዘብ ለመክፈል ፈቃደኛ ባለመሆን በቢሮው የነፃ የስልክ ቁጥር 7075 አማካኝነት ጥቆማ በመስጠታቸው ተጠርጣሪ ግለሰቦቹ እጅ ከፍንጅ ሊያዙ ችለዋል።

በቢሮው በኩልም የደረሰውን ጥቆማ መነሻ በማድረግ ከፀጥታ ኃይል ጋር በመቀናጀት ባደረገው ክትትል ጥር 1 ቀን 2018 ዓ.ም የታክስ ኦዲተር ባለሙያው ከተበዳዩ ግብር ከፋይ 50 ሺህ ብር ጉቦ ሲቀበል እጅ ከፍንጅ መያዙን አሳውቋል።

በአሁኑ ወቅት የታክስ ኦዲተር ባለሙያው በህግ ቁጥጥር ስር ውሉ ጎዳዩ በምርመራ ላይ የሚገኝ ሲሆን፥ የታክስ ኦዲት ቡድን አስተባባሪዋ ደግሞ በሠራተኞች አስተዳደር ደንብ መሰረት ከኃላፊነቷ እንድትነሳ በማድረግ ጉዳዩ እየተመረመረ መሆኑ ተገልጿል።

ቢሮው ግብር ከፋዮች መሰል የወንጀል ድርጊቶች ሲያጋጥማቸው በ7075 ነፃ የስልክ መስመር አልያም በአካል በመምጣትና በመጠቆም ሙስና እና ብልሹ አሰራር ለመቅረፍ በሚደረግ ጥረት የበኩላቸውን እንዲወጡ ጥሪ አቅርቧል።

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# ፀረ-ሙስና

## በፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በየ15 ቀን የሚዘጋጅ ጋዜጣ


ፖ.ሳ.ቁ 34799
ኢ-ሜይል FeaccEthiopia2013@et
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ፌስቡክ www.facebook.com/feaccOfficial
ቴሌግራም t.me/feacc
ትዊተር www.twitter.com/EthiopiaFeacc
ዩቲዩብ Federal Ethics & Anti-Corruption Commission


**ለሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ስራዎች**
**EARS**

---

## ለፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሙስና ወንጀል ጥቆማ መስጫ አድራሻዎች

ሞባይል 0953222255
0953222299
ፖ.ሳ.ቁ 34799
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ቴሌግራም t.me/CorruptionPointing
ዋትስአፕ wa.me/qr/5IGXTSIYUMPBF1

**NCRS**

# ርዕሰ -አንቀፅ

## ሥነምግባርን በመገንባት፣ ሙስናን በጋራ እንከላከል!

ሙስናና ብልሹ አሰራር የህብረተሰብ ልማት እንቅፋቶች ናቸው:: የመንግስትና የህዝብ ሀብትን ያሚጥጣሉ፣ ፍትህን ያዛባሉ፣ ታማኝነትንም ይጎዳሉ:: በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ተቋማት ይህንን ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ተቀናጅተው እየሰሩ መሆናቸው ተስፋ የሚሰጥ ነው::

በቅርቡ በአዲስ አበባ ፖሊስ ባስታወቀው መሰረት፣ መኪና እናስመጣለ በማለት ከ127 ዜጎች ላይ ከባድ ማታለል ወንጀል የፈጸሙ ተጠርጣሪዎች በቁጥጥር ስር ውለዋል:: ይህ ተግባር ከአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 32 ጋር ተያይዞ ከባድ የሙስና ወንጀል ተደርጎ ይቆጠራል:: በተመሳሳይ፣ በአማራ ክልል ፖሊስ ከፍትህ ተቋማት ጋር ተቀናጅቶ ባለፉት አምስት ወራት ውስጥ 556 የሙስና መዝገቦችን መርምሮ 401ዱን ወደ ክስ እያስገባ ነው:: ይህ ቅንጅታዊ ስራ የተመዘበረ ሀብት እንዲመለስና ተጠያቂነት እንዲሰፍን እያደረገ ነው::

በሌላ በኩል፣ በአዲስ አበባ ከተማ ገቢዎች ቢሮ ባለፉት አምስት ወራት የሥነምግባር ጉድለት ባላቸው 179 አመራሮችና ባለሙያዎች ላይ እርምጃ ተወስዷል:: ይህም አዳዲስ ዲጂታል ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ግልጽነትን ለመፍጠርና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የተደረገ ጥረት ነው:: በተመሳሳይ፣ የአማራ ክልል ፍትህ ቢሮ በተለያዩ ዞኖች ቢሊዮኖች ብር የተመዘበረ ሀብት በማስመለስ ላይ ትኩረት እያደረገ ነው::

እንዲሁም ታማኝነት በተግባር የሚታይበት መልካም አርአያ አለ:: የአማራ ክልል ፖሊስ አባል ኮንስታብል ሁሴን ሙስጠፋ ሰይድ በስህተት ወደ አካውንታቸው የገባውን 400 ሺህ ብር ወዲያውኑ ለአዋሽ ባንክ መልሰዋል:: ይህ ተግባር የፖሊስ ሙያ ቃል ኪዳንን በማክበር የተፈጸመ ሲሆን፣ ባንኩም የክብር ምስክር ወረቀት ሸልሟል::

ውድ ዜጎች፣ ሥነምግባር በቃል ብቻ ሳይሆን በተግባር ይገለጣል:: እያንዳንዳችን ታማኝ ሆነን በምንሰራበት ቦታ ሙስናን እንቃወም:: ተቋማት ተቀናጅተው እየሰሩ ስላሉ እኛም በግንዛቤ ተሳትፎ እናበርክት::

# ሳይቃጠል በቅጠል

## ተማሪዎች ባለመኮረጅ ሙስናን ሊታገሉ ይገባል!

ሙስና በትምህርት ተቋማት ውስጥ ያለው ችግር በኢትዮጵያ ትምህርት ሥርዓት ውስጥ ከፍተኛ ችግር ፈጥሮ ቆይቷል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የእርምት እርምጃዎችን በመውሰድ ለውጦችን ቢያመጣም የነበሩ ችግሮች ማየት አስፈላጊ ነው።

ከችግሮቹ መካከል ፈተና መቀየር፣ መግዛት ወይም በተቃራኒ በመኮረጅ ማለፍ (cheating)፣የተማሪዎች ውጤት መቀየር፣ ዲግሪ መግዛት፣ መምህራን/አስተዳዳሪዎች በገንዘብ ወይም በግንኙነት ተጽዕኖ ማሳደር፣ የትምህርት ቤት ግንባታ፣ መጽሐፍ፣ ቁሳቁስ ግዥ ላይ ብልሹ አሰራር መኖር ተጠቃሽ ናቸው።

ይህ ሙስና ትምህርትን ዋጋ የሌለው ያደርገዋል፣ የተማሪዎችን ቅንነት ያጎድላል፣ እውነተኛ ብቃት ያላቸው ተማሪዎችን ዕድል ይጋፋል። በዚህ ምክንያት ሙስናን መቃወም የትምህርት ተቋማትን ጥራት የሚያሻሽል ብቻ ሳይሆን ለወደፊት ትውልድ መልካም ምሳሌ የሚሆን ነው።

ተማሪዎች እንዴት ባለመኮረጅ ሙስናን ሊታገሉ ይገባል?

ተማሪዎች የትምህርት ሥርዓቱ ዋና ተሳታፊ ናቸው። ሙስና በተማሪዎች ላይ ቀጥተኛ ተጽዕኖ ያሳድራል። በመኮረጅ ማለፍ ሲጀምሩ ሙስናን የሚቀበሉና የሚያበረታቱ ይሆናሉ። ባለመኮረጅ መቆየት ግን ሙስናን የሚቃወም ተግባር ነው።

ቅንነት የግል ብቃትና ክብር ይጠብቃል፡ - በትክክል ተምረው ማለፍ እውነተኛ እውቀት ይሰጣል። ይህ ደግሞ በሥራ ዓለም ውስጥ ተወዳዳሪ ያደርጋል። በመኮረጅ የሚገኝ ዲግሪ ጊዜያዊ ነው፡፡

ሙስናን በተግባር መቃወም ለሌሎች ምሳሌ ለመሆን ያስችላል። አንድ ተማሪ ኩረጃን ሲጸየፍ ይህ መልካም ልምምድ በክፍል ጓደኞቹ እና ትምህርት ቤቱ ተማሪዎች ዘንድ እየሰፋ ይሄዳል። ይህ ቀስ በቀስ የተማሪዎች ባህል ወደ መሆን ያድጋል።

የአገር ዕድገት የሚጀምረው ከጥሩ የትምህርት ሥርዓት ነው። ሙስና የተሞላበት የትምህርት ሥርዓት የሚያመነጨው ብቃት የጎደለው ትውልድ ነው። ተማሪዎች ባለመኮረጅ ሲቆዩ ንጹህና ብቃት ያለው ትውልድ ይፈጠራል።

ፈተና ላይ ባለመኮረጅ መቆየት፣ የራስን እውቀት ብቻ መጠቀም፣ መምህራን ወይም አስተዳዳሪዎች ሙስና ሲፈጽሙ በተገቢው ቻናል (የትምህርት ቤት ኮሚቴ፣ የፀረ-ሙስና ቢሮ፣ የትምህርት ሚኒስቴር) ሪፖርት ማድረግ፣ በክፍል ውስጥ ቅንነትን የሚያበረታቱ ውይይቶች ማድረግ፣የተማሪዎች የስነምግባር እና የፀረ-ሙስና ክበብ/ማህበር በመመስረት ሙስናን በተቃውሞ ዘመቻ ማድረግ፣ በራስ ላይ ቅንነትን መለማመድ፣ ለሌሎች ምሳሌ መሆን፣ በአጠቃላይ ተማሪዎች ባለመኮረጅ ሙስናን ሲታገሉ የሚያደርጉት ነገር ትልቅ ነው። ይህ ተግባር ትልቅ ለውጥ ያመጣል። ሙስናን በተግባር መቃወምና ተማሪዎች ላይ መስራት የአገር ግንባታ መሠረት ነው። ቅንነትን በመምረጥ ዛሬ የምትጀምረው ትውልድ ነገ ንጹህ አገር ይገነባል።

በኢትዮጵያ የትምህርት ሥርዓት ውስጥ በቅርብ ዓመታት (በ2025 እና ቀደም ብሎ) የመውጫ ፈተና (exit exam)፣ የመግቢያ ፈተና (grade 12 national exam) እና ሌሎች ፈተናዎች ላይ በጣም ጥብቅ ክትትል ተደርጎባቸዋል። ይህም ቀደም ሲል በስፋት የነበረውን መኮረጅ (cheating) እና ሙስናን ለመቀነስ የታለመ ነው። እነዚህ ለውጦች ቢኖሩም በተፈለገው ልክ ለውጥ ለማምጣት የተማሪውም ሙስና የሆነውን ኩረጃ በመጸየፍና በመታገል የግሉን አስተዋጽኦ ማድረግ አለበት።

ታማኝነት ከሙስና ይበልጣል!

ተማሪ ሆይ፣ ባለመኮረጅ ጀምር፣ ሙስናን አሸንፍ! የሚል መልዕክት እናስተላልፋለን።

## ከሙስና ምርመራ ዘገባ ማህደር

በዚህ አምድ በዋናነት ትኩረት የሚደረገው ማንኛውም የመንግስትና የህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የማይገባ ጥቅም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው በማስገኘት እና በሌላ ሰው መብት ወይም ጥቅም ላይ ጉዳት በማድረስ በተሰጠዉ ኃላፊነት ከሌላ ሰው ላይ ጥቅም የተቀበለ፣ የጠየቀ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ጥቅም በማስገኘት የተሰጠዉን ስልጣን፣ የህዝብ አደራ ያላአግባብ የተገለገለ፤ ለሌላ ሰው ያስገኘ፣ በሌላ ሰው መብት ወይም ጥቅም ላይ ጉዳት እንዲደርስ በማድረግ ለመንግስትና ለህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ የማይገባ ጥቅም የሰጠ፣ ያቀረበ እንደሆነ፤ በአግባቡ ለተፈጸመ የመንግስት መስሪያ ቤት፣ የመንግስት ልማት ድርጅት እና የህዝባዊ ድርጅት ስራ የማይገባ ጥቅም ለማንኛውም ሰዉ የሰጠ፣ ከማንኛዉም የመንግስት እና ህዝባዉ ድርጅት ሰራተኛ የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ፈጻሚነት ተጠያቂ በመሆን በምርመራ የሙስና ወንጀል ፈፅመው የተገኙ አካላትን በማጠናቀር መረጃዎችን ለአንባቢያን ተደራሽ የሚደረገበት



ነው።

በመሆኑም በሕገ ወጥ መንገድ ገንዘብ በማስተላለፍ ኢትዮጵያ ከ13 ሚሊየን ዶላር በላይ እንድታጣ በማድረግ የተጠረጠረው ግለሰብ በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 2ኛ ልዩ ልዩ ጉዳዮች ወንጀል ችሎት ክስ ቀረበበት። ተከሳሹ ነጋሲ ተስፋልደት በ2017 ዓ.ም የወጣውን የባንክ ስራ አዋጅ ቁጥር 1360/2017 አንቀጽ 2 (6) (መ) ፤ 3 (1) እና 90 (1) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ የወንጀል ድርጊት መፈጸሙን በመግለጽ ነው ዐቃቤ ሕግ ክስ ያቀረበው።

ተከሳሹ የባንክ ስራ ለመስራት ከብሄራዊ ባንክ የተሰጠ ህጋዊ ፈቃድ ሳይኖረው ለጊዜዉ ካልተያዙ ግብረአበሮቹ ጋር በመሆን በተለያዩ የውጭ ሀገራት የሚገኙ ግለሰቦች ገንዘብ ወደ ኢትዮጵያ ለመላክ ሲፈልጉ የሚላክላቸውን ሰዎች ስም ዝርዝር፣ የባንክ ሂሳብ ቁጥር እና የገንዘብ መጠን በሚያስተላልፉለት መረጃ መሰረት ገንዘቡን ኢትዮጵያ ውስጥ ላሉ የተለያዩ ግለሰቦች በስሙ ከከፈታቸው የባንክ ሂሳቦች ገንዘብ ማስተላለፉ በክሱ ተመላክቷል።

በአዋሽ ባንክ ተከሳሹ በስሙ በከፈተው የሂሳብ ቁጥር ከ2012 ዓ.ም እስከ 2018 ዓ.ም ድረስ 578 ያህል ጊዜ 110 ሚሊየን 594 ሺህ 572 ብር ለተለያዩ ግለሰቦች አስተላልፏል ሲል ዐቃቤ ሕግ ጠቅሶ፤ ይህ ገንዘብ በህጋዊ አስተላፊዎች አማካኝነት ቢተላለፍ ሀገሪቱ 1 ሚሊየን 622 ሺህ ዶላር ታገኝ ነበር ብሏል። እንዲሁም በአቢሲኒያ ባንክ በስሙ በከፈታቸው የሂሳብ ቁጥሮች ከሰኔ 11 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሕዳር 4 ቀን 2018 ዓ.ም ድረስ 1 ሺህ 153 ጊዜ በአጠቃላይ 242 ሚሊየን 194 ሺህ ብር ለተለያዩ ግለሰቦች ገንዘብ አስተላልፎ በሕጋዊ አስተላላፊዎች በኩል ቢላክ ሀገሪቱ የምታገኘውን 3 ሚሊየን 469 ሺህ 923 ዶላር ማሳጣቱ በክሱ ተገልጿል።

እንዲሁም ተከሳሹ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በስሙ በከፈታቸው የሂሳብ ቁጥሮች በመጠቀም ከጥር 17 ቀን 2013 ዓ.ም እስከ ሕዳር 4 ቀን 2018 ዓ.ም ድረስ 2 ሺህ 710 ጊዜ በአጠቃላይ 540 ሚሊየን 274 ሺህ ብር ለተለያዩ ግለሰቦች በማስተላለፍ በህጋዊ ገንዘብ አስተላላፊዎች አማካኝነት ቢላክ ሀገሪቱ የምታገኘውን 6 ሚሊየን 336 ሺህ 300 ዶላር ማሳጣቱን ዐቃቤ ሕግ አብራርቷል።

ተከሳሹ ፍቃድ ሳይኖረው በአጠቃላይ 1 ቢሊየን 1 ሚሊየን 400 ሺህ ብር ከውጭ ሀገራት ገንዘብ ለተላከላቸዉ ሰዎች በማስተላለፍ ገንዘቡ በህጋዊ ገንዘብ አስተላላፊዎች አማካኝት ወደ ሀገር ቢላክ ኖሮ ኢትዮጵያ ታገኝ የነበረውን 13 ሚሊየን 31 ሺህ 200 የአሜሪካ ዶላር አሳጥቷል ያለው ዐቃቤ ሕግ፤ ያለ ብሔራዊ ባንክ ፍቃድ የባንክ ስራ በመስራት ወንጀል ግለሰቡ ላይ ክስ አቅርቧል።

# መልካም ዜጋ

## የታማኝነት ተምሳሌት ሳጅን ዋሲይሁን በፈቃዱ

የጋሞ ዞን ፖሊስ መምሪያ አባል ሳጅን ዋሲይሁን በፈቃዱ በቅርቡ በስህተት ወደ ባንክ አካውንታቸው የገባውን 145,290 ብር (አንድ መቶ አርባ አምስት ሺህ ሁለት መቶ ዘጠና ብር) ሙሉ በሙሉ ለባለቤቱ አቶ ይልቃል ዘውዴ ተሰማ መልሰው ሰጥተዋል።

ገንዘቡ በስህተት እንደገባ እንደተረዱ በዚያው ቀን ሳያመነቱ መመለሳቸው በተለይ በአሁኑ ጊዜ ብዙ ሰዎች ተመሳሳይ ሁኔታ ሲያጋጥማቸው ራሳቸውን ማስተካከል ሲቸገሩ፣ ይህ ተግባር ትልቅ አድናቆት አስገኝቷል።

ሳጅኑ እንደተናገሩት "የደንብ ልብስ ለብሼ የምጠብቀው የህዝብን ሰላም ብቻ ሳይሆን የህዝብን ንብረትም ጭምር ነው"።

ይህ ድርጊት ለሌሎች ፖሊስ አባላት፣ ለህብረተሰቡ እና ለወጣቶች ትልቅ ትምህርት ሆኗል። ባለቤቱ አቶ ይልቃልም በጣም ተደስተው



በስህተት ወደ አካውንቱ የገባውን 145 ሺህ 290 ብር የመለሰው ሳጅን

ምስጋናቸውን ገልጸዋል።

በፌስቡክ፣ ቲክቶክና ሌሎች መድረኮች ላይ ብዙ ሰዎች "ክብር ለታማኙ ፖሊስ!" ብለው እየተወያዩ ነው። እንዲህ ያሉ የመልካም ዜግነት ምሳሌዎች ሲበዙ ህብረተሰቡ የበለጠ ይጠነክራል።

በተመሳሳይ መረጃ በአዲስ አበባ አያት አካባቢ ነዋሪ የሆነችው ወጣት እመቤት መኮንን ያልጠበቀችው በስልኳ 300,000 (ሶስት መቶ ሺህ) ብር ወደ ሂሳብ አካውንቷ በስልኳ መልዕክት መግባቱን ተናግራለች።

ገንዘቡ የሷ እንዳልሆነ ያወቀችው እመቤት ለአፍታም ሳታመነታ "ይህ የሰው ሀቅ ነው፤ የኔ አይደለም!" በማለት ለራሷ ወሰነች።

ከደቂቃዎች በኋላ ገንዘቡን በስህተት የላከውና በአላማጣ ከተማ የሚኖረው ወጣት መሐመድ መኪ ደውሎ ሲያናግራት፤ በፍጥነት እና በቅንነት ገንዘቡን ለመመለስ ተባበረችው።

"እኔም በላቤ የምኖር ሰው ነኝ። ሰው በላቡ ለፍቶ ያገኘውን ገንዘብ በስህተት ወደ ሌላ ሰው መላክ ሊያጋጥም ይችላል፤ የራስ ያልሆነን ነገር መመለስ ግን ለኅሊና ዕረፍት ነው" ብላለች።

ከአላማጣ ሆኖ በጭንቀት ይደውል የነበረው መሐመድ በበኩሉ በወጣቷ ምላሽ ተደናቋል። "ደውለን ስናናግራት የሰጠችን ምላሽ እምነቷንና ታማኝነቷን እንድገነዘብ አድርጎኛል። አላህ ሀቋን ይክፈላት" ሲል መርቋታል።

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

## የሀዘን መግለጫ

የኮሚሽናችን የሥራ ባልደረባ የነበሩት አቶ ወንድይራድ ሰይፉ ከዚህ ዓለም ድካም አርፈዋል። በዚህም ኮሚሽኑ የተሰማውን ጥልቅ ሀዘን እየገለጸ ለቤተሰቦቻቸው፣ ለወዳጅ ዘመዶቻቸው፣ ለኮሚሽኑ አመራርና ሰራተኞች መጽናናትን ይመኛል።










የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን አመራሮች እና ሰራተኞች

# ኪነ-ጥበብ

## ትልቁ ምሰሶ!

መሠረት የሆነ ለመቅረጽ ትውልድን ፣
ለኢኮኖሚ እድገት ለማልማት ሀገርን፣
ፍቅርን ለመገንባት ለማምጣት ሰላምን፣
ትልቁ ምሰሶ ትልቁ መሠረት፣
ለእድገት ብልጽግና ዋናው የሀገር ሀብት፣
ፍቅርን ትብብርን ሁሉንም ለማምጣት፣
ሰው በላቡ ሠርቶ ለማደግ ባንድነት፣
ትልቁ መነሻ ትልቁ አንገብጋቢ፣
የህይወት መንገዱ ዋናው አሳሳቢ፣
የሰዉ ልጅ ምግባር ነው ሁሉንም ሰብሳቢ::
አንተ ትብስ ብሎ ተዋዶ ለመኖር፣
አክብሮ ተከብሮ ለመኖር በፍቅር፣
ትውልድን ለማፍራት የሚሆን ለሀገር፤
ለሰው ልጆች ሁሉ ምሰሶ ነው ምግባር::
ትልቁ ፍጡር ሰው ምግባር ከጎደለው፣
ጥሩና መጥፎውን መለየት ካቃተው፣
መሠረቱን ለቆ መሠረት ከሌለው፣
ከፍጥረት ይጎላል፣
መዋል ከሌለበት ከሌሎች ይውላል፣
እራሱን ይጥላል፣
የራሱ ያልሆነን የተከለከለ በለሱን ይበላል፣
መጣል ከሌለበት በስራው ይጣላል::
እናም .........
ለህይወት መነሻ ቀዳሚ ውጥኑ፣
የሰው መሰረቱ ምግባር በመሆ፣
ምሰሶውን ያዙ ባለምግባር ሁኑ::

**ከያብባል አዲስ**